# ኢሕአፓን ማሰባሰብ ማለት ምን ማለት ነው?

ከንጋቱ አየለ

ኢሕአፓን ለማሰባሰብ የሚለው አባባል ያለ ጥርጣሬ ከተስተዋለ ማልካም ይመስላል፡፡ በሌላ መልኩ ግን ኢሕአፓ ፍርክስክሱ ስለወጣ መልሰን እንሰባሰብ የሚል ሕዝብን የሚያሳዝንና ጠላትን በተለይም ወያኔን የሚያስፈነጥዝ መልዕክት አለው፡፡ እኔ እንደማውቀው የዛሬ 43 ዓመት የተመሰረተው ኢሕአፓ የትግሉን ውጣ ውረድ መክቶ ዛሬም ከጸረ- ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር ግብግብ ላይ ነው ያለው፡፡ የኢሕአፓ ጠላቶች ብዙ ናቸው፡፡ የዛሬው ዋና ጠላቱ የኢትዮጵያ ጠላት የሆነው ወያኔ ስለመሆኑ ማብራሪያ መስጠት አያስፈልግም፡፡ ኢሕአፓ ከውጭ ጠላቶቹ ባልተናነሰ የራሱ የነበሩ አባላቱ ከድተው የጥቃት ብቀላ አዝንበውበታል፡፡ የድሮዎቹን ለታሪክ እንተውና ከስምንት አመት ወዲህ ድርጅቱን ለማፍረስ ወያኔ የሰጣቸውን ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ የተሰማሩ ግን ፕሮጀክታቸው እንደ ባቢሎን ግንብ የፈራረሰባቸው በስማችን መጨረሻ ዴ የሚል ፊደል በመጨመር ሕዝቡ ለማደናገር ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ይህ ቡድን ላለፉት ስምንት ዓመታት ወያኔን ከመታገል ይከቅ ሃቀኛውን ኢሕአፓን በሕዝብ ለማስጠላት ከንቱ ድክመት ሲያደርጉ ሰንብተዋል፡፡ የሚገርመው ግን የተፈጥሮ ባሕሪያቸው ሆኖ ያችው 20 የማትሞላው ቁጥራቸው የበዛ ይመስል ሁለት ሶስት ቦታ ተሰነጣጥቀው ሕልውናቸው ጠፍቷል፡፡

ጥቂት ቁጥር ያላቸው ደግሞ የኢሕአፓን ደንብ አልከተልም ያሉና የዘርም ደም ያጃጃቸው ከድርጅቱ በመባረራቸው ቀደም ሲል ዲያብሎስ ብለው ከሰየሙት አንጃ ጋር ፍቅር ይዘዋል፡፡ ሁሉም ጋጠወጥና የዲሞክራሲ ባላንጣ በመሆናቸው ጋብቻቸው አድሜ ቢስ መሆኑን መገመት አያዳግትም፡፡ ቁጥር ጥሩ ነው ምክንያቱም ሃቅን ያጎላልና ዴዎች አባሎች አሉኝ ካለ 12 አይሆኑም፡፡ የእርምት እንቅስቃሴ የሚለው ደግሞ 5 አባላት ካሉት ተዐምር ነው፡፡ ከሞት የተነሳው ትንሳኤ ደግሞ 3 ናቸው፡፡ ይህ ቁጥር ካንድ አመት በፊት የነበር ስለሆነ በዛሬው ወቅት እንዳለ ለመሆኑ ቃል አልገባም፡፡ ቢያንስ ግን 20% ከመጀመሪያ ቁጥራቸው ይቀንሳሉ የሚል ግምት አለኝ፡

እነዚህ ከኢሕአፓ የሸሹና በማጋጣ ዲሲፕሊን የተገለሉት ኢሕአፓን ለማጥፋት ቆርጠው ተነስተዋል፡፡ አንዳንዱ የ 8 ዓምት ቁርሾ አለው፣ አንዳኑ ደግሞ የ3 ዓመት ጥላቻ አለው፣ ሌላው ደግሞ የ35 ዓመት የማጥፋት ዓላማው ያልተሳካለት ከዚህ ስብሰብ ውስጥ አለ፡ ፡ ለነሱ ዋናው ጠላታቸውና ትኩረታቸው ኢሕአፓን ማጥፋት እንጅ ከወያኔ ጋር መታገል አይደለም፡፡ ወደፊት በግልጽ ሊወጣ የሚችል እነሱ በሚስጢር የያዙት የሚመስላቸው ወያኔያዊ ተልዕኮአቸው ግልጽ የሚሆን ጉዳይ አለና ሁኔታው ሲፈቅድ ይወጣል፡፡

እኔ የማውቀውና ያለሁበት ድርጅት አንድ ኢሕአፓና አንድ ኢሕአፓ ብቻ መሆኑን ነው የማውቀው፡፡ ሰማይና ምድር ይገለባበጣሉ እንጅ እነዚህ ጉግ ማንጉንች የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሃብቱ የሆነውን የሆነውን ኢሕአፓ በምንም ዓይነት ሊጠልፉና ለወያኔ ግብር ሊሰጡ አይችሉም፡፡ እነዚህ ቂሎች ኢሕአፓን እጁን ጠምዝዘን እንቆጣጠረዋለን ብለ ሲባክኑ ይሞታሉ እንጁ ወይ ፍንክች ይላሉ ጀግናዎቹ የኢሕአፓ አባላት፡፡

ዘንድሮ ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ ሲምፓዚየም አዘጋጅተናል ብለውናል፡፡ ሲምፖዚየም ማለት ጉባኤ ነው፡፡ በርግጥ በፈረንጅኛው መጠቀሱ የተማሩ የተመራመሩ የሚያደግርጋቸው ስለሚመስላቸው መርጠውታልና ይመቻቸው፡፡ የስብስባቸው ተናጋሪ እንግዳዎች በሙሉ ለኢሕአፓ ቀና የማያስቡ ናቸው፡፡ በተለይ የቦዘኔነት ባሕሪ የተላበሰው ታዘበው፣ ድርጅቱን የዛሬ 30ዎቹ አመት የከዳው ክፍሉ ታደሰና ኢሕአፓን ለወያኔ ገጸ በረከት አቀርባለሁ ያለው አንጃ መሪው መርሻ ዮሴፍ ስም ማየቱ ስብስቡ ምንኛ ተንኮል ያዘለ ስለመሆኑ ምርምር አይጠይቅም፡፡

ከዚህ በፊት እርቀሰላም በማለት ወደ ድርጅቱ ወገንተኝነታቸው የዴዎች የነበሩ ሽማግሌዎች በድርጅቱ ላይ ጫና ለመፍጠር ሞክረው ነበር፡፡ ቀላል ሽማግሌዎች በመሆናቸው ሙከራቸው መና ሆኖ የእፍረት ሽማቸውን ተከናንበው ወደ መጡበት ሃሜታቸውን ለመዝራት ተበትነዋል፡፡ ሲምፓዚየሙ ወድ 6 የሚጠጉ ዶክተሮችን ቀጥሮ ጸረ-ኢሕአፓ የሆነ ፈንጅ ቦንብ እንዲፈጥሩ አሰማርቷል፡፡ ኢሕአፓን ለማጥፋት የሚፈጥሩት ፈንጅ የራሳቸው መጥፊያ ይሆናል፡፡ ዶ/ር ድምሴ ኡላሜ (ደምሴ ዶ/ር መሆንዎን አላውቅም ነበር)፣ ዶ/ር መላኩ፣ ዶ/ር አበባ፤ ዶ/ር ሙሉጌታና ዶ/ር ፍጹም ይህ ጸረ-ኢሕአፓ ተግባራችሁ ካዋጣችሁ በቀጣዩ ጽሁፌ ስለ እያንዳንዳችሁ ገድል መጻፌ እንደማይቀር ይገንዘቡ፡፡ ለምን በጣም ብዙ ዶክተሮች ጸረ ኢትዮጵያ አመለካከት ሊኖራቸው ቻለ ለሚሌው ጥያቂ የሚመልስልኝ ሰው ቢኖር ምስጋናዬ የላቀ ይሆናል፡፡

ይህን ጽሁፍ ያነበባችሁ ኢትዮጵያውያን ልብ ይበሉ፡፡ እነዚህ ጸረ ኢሕ አፓ ግን አፍቃሪ ወያኔዎች የሚቀጥለው እመት ሲምፓዚዮሙን ትተው ኮንፍረንስ፡ ኮንግረስ ወይም ዎርክሾፕ ..... ብለው እንደሚጠራችሁና ያኔም ወያነነ እንታገል ሳይሆን ኢሕ አፓን አንድ እናድርግ የሚል አዘናጊ ሴራቸውን እንደሚቀጥሉ አትጠራጠሩ፡፡ ከዋሸሁ የሚቀጥለውን አመት ትታችሁ የዛሬ ሁለት አመት ይህ ጥሪ እንደሚያጋጥማችሁ ልነግራችሁ እፍርልጋለሁ፡፡ ሀቁ ግን አፍቃሪ ወያኔ የሆኑት እነዚህ አንጃዎችና በታኞች ዛሬ ክፍሉ ታደሰን ይዘው እንደቀረቡ በመጭው ዓመት ታምራት ላይኔን ይዘው የማይመጡበት ምክንያት የለም፡፡ ዘንድሮ ለምን የእርምት ንቅናቄው በረከት

ስሞንን ያልጋበዘበት ምክንያት አልገባኝም፡፡ ይህን ሁሉ ብዬ ይህ ጸረ ኢሕ አፓ ቡድን ምንኛ የወያኔ ወዳጅ መሆኑ ካልገባችሁ በትግሉ ውስጥ አንድ ችግር አለ ማለት ነው፡፡ አልኩትም አላልኩት ወያኔ መውደሙ አይቀሬ ነው፡፡ አሳፋሪዎቹ አንጃዎችና ባንዳዎች ላንዴና ለመጨረሻ መመታት አለባቸው፡፡

ኢሕአፓ አንድና አንድ ብቻ ነው!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባስመሳይ አንጃዎች አይወናበድም!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!